# ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
# የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተሠጠ መግለጫ

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም "ለቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የላዕላይ ም/ቤት" በሚል በአቶ ሀይሉ ሻውል ደብዳቤ ተጽፎ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ ሆኗል።

ደብዳቤው "...ቅንጅትን ለመመስረት እጅግ ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማለፍ የግድ ነበር። በወቅቱ ትግሉ የጠየቀውን የአንድነትና የህብረት ጥያቄ መመለስ ተገቢ በመሆኑ ከድርጅት ጥቅም አንጻር ሳይሆን ከኢትዮጵያችን የወደፊት ጥቅም ጋር በማገናዘብ ቅንጅት እንዲፈጠር በሙሉ ፈቃደኝነትና ፍላጎት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ይህ በቅን ልቦና የተደረገዉ ጥረታችን ያስገኘው ውጤት ግን በተቃራኒዉ ነው...ይህ ሁሉ ጥረታችንና ቅንነታችን ግን እንደ አላዋቂ ከማስቆጠር፣ የአንዳንዶችን ድብቅ አላማ ማስፈጸሚያ ከመሆን፣ ለውግዘትና ለስድብ ከመዳረጉ ሌላ ያተረፈልን ነገር የለም።አንዳንድ ግለሰቦች ቀድሞውኑ ለትግሉ በቅንጅት መስራት አስፈላጊ መሆኑን በመስበክና የህዝቡን የአንድነት መንፈስ እንደሽፋን በመጠቀም የትግሉን አቅጣጫ ለማስቀየር ካልተቻለም ራሳቸውን የትግሉ መሪ ለማድረግ ጽኑ ፍላጎት እንደነበራቸውና ለዚህም ሴራ እየጎነጎኑ ለመሆኑ ጥቆማዎች የደረሱን ቢሆንም ሁሉን ችለን ታግሰናል። ትግሉ አንድ እርከን ከፍ እንዲልም የበኩላችንን አስተዋጽኦ አድርገናል። እነዚህ ግለሰቦች ድብቅ አላማቸውን በከፊል ለማስፈጸም መጣር የጀመሩት አመራሩ ለወህኒ በተዳረገበት ወቅት ለመሆኑ መረጃዎች አሉን።" ሲል አትቶ እነዚህ ግለሰቦች የትግሉን አቅጣጫ ለማስቀየርና አመራሩን በሴራ ለመንጠቅ የተለያዩ ድርጊቶችን ፈጽመዋል በሚል ባለ 20 ነጥብ ውንጀላዎችን አስፍሯል።

በማስከተልም ደብዳቤው የቅንጅት የላዕላይ ም/ቤት እንዲያስፈጽማቸው አራት ትዕዛዞችን አስተላልፏል። ከእነዚህም መካከል "በአሁኑ ወቅት የቅንጅትን ህግና ደንብ በመጻረር ቀን በቀን በመንቀሳቀስ የድርጅቱን ህልውና ጭምር አደጋ ላይ እንዲወድቅ ከፍ ያለ ሚና እየተጫወቱ ነው" በሚል እርሳቸዉ በሀላፊነት ቦታቸዉ ላይ በሌሉበት በአሁኑ ወቅት በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት ድርጅቱን በበላይነት በሀገር ቤት በመምራት ላይ የሚገኙትን የድርጅቱን ተቀዳሚ ም/ሊቀ መንበር ጨምሮ አምስት የድርጅቱን ከፍተኛ አመራር አባላት በድርጅቱ ስም እንዳይንቀሳቀሱ ማገድ ዋነኛው ነው።

የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የድርጅቱን ሃላፊዎች የሥራ አፈጻጸም የመከታተል እና የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው በመሆኑ ታህሳስ 3/2000 ዓ.ም ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ፓርቲው የገጠመውን ችግር የማባባስ ውጤት ሊኖረው የሚችለውን ይህን ደብዳቤ በጥልቀት ተወያይቶበት የሚከተሉት ውሳኔዎች ላይ ደርሷል።

ሀ) በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀ መንበር በአቶ ሀይሉ ሻውል ታህሳስ 1/2000 ዓ.ም ለቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የላዕላይ ም/ቤት የተጻፈው ደብዳቤ ሊቀ መንበሩ ከሚገኙበት የውጭ ሀገር በቀጥታ ለመገናኛ ብዙሃን ከተሰጠ በኋላ የላዕላይ ም/ቤቱ አባላት ጉዳዩን እንዲያውቁት መደረጉ ምን ሥርዓትን ያልተከተለ አካሄድ መሆኑን የቅንጅት ሥ/አስፈጻሚ ኮሚቴ ያስገነዝባል።

ለ) አቶ ሀይሉ ሻውል በአሁኑ ወቅት የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀ መንበር ሆነው ሳለ በደብዳቤያቸው መግቢያ ላይ መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት የከሰመው የቀድሞ መኢአድ ዛሬም እንዳለና እራሳቸውንም የውሁዱ ቅንጅት ሳይሆን የከሰመው ድርጅት መሪ ማስመሰላቸዉ ከፍተኛ ስህተት መሆኑን የቅንጅት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያስገነዝባል።

ሐ) አቶ ሀይሉ ሻውል በደብዳቤያቸው በአንዳንድ ግለሰቦች ተፈጸሙ ያሉአቸውን የተለያዩ ባለ ሃያ ነጥብ "ጥፋቶች" ከዘረዘሩ በኋላ የቅንጅት የላዕላይ ም/ቤት እንዲያስፈጽማቸው አራት ትዕዛዞችን አስተላልፈዋል። ከእነዚህም መካከል "በአሁኑ ወቅት የቅንጅትን ህግና ደንብ በመጻረር ቀን በቀን በመንቀሳቀስ የድርጅቱን ህልዉና ጭምር አደጋ ላይ እንዲወድቅ ከፍ ያለ ሚና እየተጫወቱ ነው" በሚል ሰበብ

1ኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን
2ኛ ኢ/ር ግዛቸዉ ሺፈራውን
3ኛ ዶ/ር ሀይሉ አርአያን
4ኛ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን እና
5ኛ አቶ ብሩክ ከበደን

"በቅንጅት ስም ከመንቀሳቀስ እንዲታቀቡ" ሲሉ ያስተላለፉት የእግድ ትዕዛዝ የሚጠቀስ ነው። የቅንጅት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እነዚህን የአቶ ሀይሉ ሻዉልን ትዕዛዞች በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ስለ ድርጅቱ ሊቀ መንበር ሥልጣንና ተግባር ከሚዘረዝረዉ አንቀጽ 25 እና የድርጅቱ አመራር አባላት ከድርጅቱ ስለሚታገዱበት ሁኔታ ከሚገልጸዉ አንቀጽ 10/3 ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ በድርጅቱ ሊቀ መንበር በአቶ ሀይሉ ሻውል የተላለፉት አራት ውሳኔዎች የድርጅቱን ህገ ደንብ የጣሱ፣ የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ለድርጅቱ ሊቀ መንበር ከሚሰጠው ሥልጣን ውጭ የተፈጸሙና ከጠቅላላ ጉባኤ ቀጥሎ የድርጅቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ለሆነው የቅንጅት ላዕላይ ም/ቤት ያለ አግባብ ትዕዛዝ የሰጡ ሆነው አግኝቷቸዋል።

በተጨማሪም ይህን ሥርዓት ያልተከተለ አካሄድ የተቀበሉ የቀድሞ መኢአድ አባላት የነበሩ ጥቂት የላዕላይ ም/ቤት አባላትም የሥራ አስፈጻሚው ስብሰባ በድርጅቱ ጽ/ቤት እንዳይካሄድ አደናቅፈዋል። የቅንጅቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የድርጅታቸው ቢሮ ተዘግቶባቸው በጥበቃ ሠራተኞች እንዲመለሱ ተደርገዋል። ይህም ከፍተኛ ጥፋት መሆኑን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያስገነዝባል።

መ) አቶ ሀይሉ ሻውል በደብዳቤያቸው "ከድርጅታችን ህግና ደንብ ውጭ የድርጅቱን የትግል አቅጣጫ ለማስቀየርና አመራሩን በሴራ ለመንጠቅ" ሞክረዋል በኋቸው የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ላይ ያቀረቧቸውን ባለ 20 ነጥብ ውንጀላዎች የድርጅቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መርምሮ አንዳንዶቹን ፍጹም ሀሰተኛ ክሶች፣ አንዳንዶቹን ደግሞ በተራ አሉባልታ ላይ የተመሰረቱ ውንጀላዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ ራሳቸው አቶ ሀይሉ ሻውል የተስማሙባቸውና በፊርማቸው ያጸደቋቸው ድርጅታዊ ውሳኔዎች መሆናቸውን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ታስበው የተሰነዘሩ እንደሆኑና ቀሪዎቹ ደግሞ የዴሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብ መሰረት በሆነው የጋራ አመራር መርህ ለመመራት ፈቃደኛ ካለመሆንና ከአምባገነናዊ አስተሳሰብ የሚመነጩ ሆነው አግኝቷቸዋል።

ሠ) ሊቀ መንበሩ በአብዛኛዉ የአመራር አባላት ድምጽ ለተወሰኑ ድርጅታዊ ውሳኔዎች ባለመገዛት በራሳቸዉ ሀሳብ ሲራመዱ ይህ የመጀመሪያቸው አይደለም። ለአብነት ያህል የፓርቲው አብዛኛው አመራር ከመታሰሩ አስቀድሞ ፓርቲው ውሳኔ ያልሰጠበትን ጉዳይ እንደወሰነበት በማድረግ የራሳቸውን ሀሳብ እንደፓርቲው የመጨረሻ አቋም አድርገው ሲገልጡ ቆይተዋል። በተጨማሪም በሊቀ መንበሩ በራሳቸው በተደጋጋሚ እንደሚገለጸው በእስር ቤት ቆይታችን አብዛኛው አመራር አባል ከተስማማበት ውጭ በሌላቸው ሥልጣን ዓለምአቀፍ አመራር ምክር ቤት አቋቁመው እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይህም ለጋራ አመራር መርህ የማይገዙ መሆናቸውን ያሳየ ተግባር እንደነበረ ሥራ አስፈጻሚው ተገንዝቧል።

ረ) ይህ በዋናነት በሊቀ መንበሩ እና በጥቂት የአመራር አባላት እየተፈጸመ ያለው ከድርጅቱ የዴሞክራሲ አሰራር እና ህገ ደንብ የወጣ ተግባር ተገቢው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለላዕላይ ም/ቤቱ የሚያቀርብ መሆኑን እየገለጸ አቶ ሀይሉ ሻውልም ሆኑ ቅንጅትን በማፍረስ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሌሎች ግለሰቦች ሁሉ ከእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር እንዲታቀቡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ወስኗል።

በመጨረሻም የቅንጅት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀጣይ የፓርቲውን እንቅስቃሴዎች በተከታታይ ለህዝብ እንደሚያሳውቅ ይገልጻል።

የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
ታህሳስ 4/2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ